## ደረጃ 4

**ተማሪዎች ስለ ግል ትምህርታቸው ያላቸውን ግንዛቤ እና ኃላፊነት ለማሳደግ፣ የአስተሳሰብ ሂደትን በሚመዝኑ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲሳተፉ**

### ይህ ምን ማለት ነው?

ይህ ማለት ተማሪዎች ስለ ግል ትምህርታቸው ኃላፊነት አለባቸው ማለት ነው። በመሆኑም ተማሪዎች የሚማሩት ምን እንደሆነ፣ እንዴት እየተማሩ እንደሆነ እና ለትምህርታቸው እንዴት ግብ ማውጣት እንዳለባቸው ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይጠበቃሉ።

### ልጅዎን እንዴት መርዳት ይችላሉ?

ከልጅዎ ጋር ሆነው ምን እየተማረ፣ እንዴት እየተማር እንደሆነ እና ርዕሰ ጉዳዩ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ይወያዩ።

ልጅዎ ጥንካሬዎቹን እና መሻሻል የሚፈልጉ አካባቢዎችን የሚያሰፍርበት ሰንጠረዥ እንዲያዘጋጅ ያድርጉ። ከልጅዎ ጋር የአካደሚክ ግቦችን ይንደፉና የእድገት ሂደቱን በየጊዜው ይከታተሉ።

ለምሳሌ: በቤት ሥራ መልክ ልጅዎ በየምሽቱ አንድ ምዕራፍ እንዲያነብ ግብ ካዘጋጁ፣ ልጅዎ የየዕለቱን ዕድገት በሰንጠረዥ፣ በማስታወሻ ደብተር ወይም በቀን መቁጠሪያ ላይ በማስፈር እንዲከታተል ያድርጉ።

የኢንፍኒት ካምፐስ ድረገጽ ላይ የወላጆች ገጽን በመጎብኘት የልጅዎን የፈተና ወጤትና ደረጃ፣ የክፍል ተሳትፎ(አቴንዳንስ)፣ የአካደሚክ እድገት፣ ሪፖርቶች፣ ወዘተ ማየት ይችላሉ። ይህን መረጃ በመጠቀምም ከልጅዎ ጋር በመሆን ግቦችን ይንደፉበት።

ልጅዎ ስለ አንድ ነገር ለማወቅ ጉጉት ሲኖረው አብረውት በመስራት ስለ ጉዳዩ ከኮምፒዩተር ላይ በማሰስ፣ በቤት ውስጥ ወይም በመጸሐፍት ቤት የሚገኙ ምንጮችን በመጠቀም መልሱን ያፈላልጉ።

እርስዎ ለማያውቋቸው ነገሮች መልስ ለማግኘት የተጠቀሙባቸውን ሂደቶች ለልጅዎ ያሳዩ።

## ደረጃ 5

**ምዘና ከመመሪያ ጋር የተሳሰረ ነው**

### ይህ ምን ማለት ነው?

ይህ ማለት ተማሪዎች ስለሚማሩት ትምህርት ጽንሰ ሃሳብ በሚገባ እየተማሩ መሆኑን ለማረጋገጥ ተከታታይ የሆነ ክትትል ይደረግባቸዋል ማለት ነው። በመሆኑም ተማሪዎች ምን እየተማሩ እንደሆነ እና ለምን እንደሚማሩትም ጭምር ማብራራት ይችላሉ።

### ልጅዎን እንዴት መርዳት ይችላሉ?

የልጅዎን የትምህርት ሁኔታና እድገት የኢንፍኒት ካምፐስ ድረገጽን በመጠቀም ይከታተሉ። ልጅዎ እንዲሰራቸው የተሰጡትን የክፍልና የቤት ሥራዎች አጠናቆ ካላስረከበ ወይም ፈተናውን ከወደቀ፣ ከልጅዎ ጋር አብረው ሆነው የሚሰጡትን ሥራዎች ለማጠናቀቅ እና ደረጃውን ለማሻሻል የሚረዳ ግብ አቅዱ።

ወደ ቤት የሚላክልዎን የልጅዎ የትምህርት ደረጃ መግለጫዎች እና ሪፖርቶች በተወሰነው ጊዜ ይመልሱ፤ ጥያቄዎች ካለዎት ለአስተማሪው በማስታወሻ አካተው ይላኩ።

ከፈተና በፊት የልጅዎን የማስታወሻ ደብተር ለማየት ዕቅድ ያውጡ። ከማስታወሻ ደብተሩ ላይ ጥያቄ እያወጡ ይጠይቁ፤ በተጨማሪም ልጅዎ ፈተና ላይ ሊመጡ ይችላሉ ብሎ የሚያስባቸውን ጥያቄዎች በጽሑፍ እንዲያሰፍራቸው ይጠይቁ። ከፈተናው በኋላ ስለ ፈተናው ሂደት እና ውጤት ከልጅዎ ጋር ይወያዩ።

ከልጅዎ አስተማሪ ጋር በመደበኛነት መረጃ ይለዋወጡ፣ በተጨማሪ ልጅዎን በትምህርት እቅድ ዝግጅት ውስጥ ያሳትፉ።

ለምሳሌ: ከመምህሩ ጋር ዕለታዊ እና ሳምንታዊ ዕቅድ ማስፈሪያ በመጠቀም መረጃ ይለዋወጡ።

የትምህርት ቤትዎን ድረገጽ ከccsd.net፣ የ"ፌስስ" ድረገጽን ደግሞ ከfaces.ccsd.net አዘውትረው በመጎብኘት ተጨማሪ የመማሪያ መሳሪያዎች እና ጠቃሚ የፈተና ቀናቶችን ይመልከቱ።




# የቤተሰብ መመሪያ



ተማሪዎችን በመኖሪያ ቤታቸው ለማገዝ የተዘጋጀ

ለተጨማሪ መረጃ :በሚከተሉት የመገናኛ መንገዶች ያግኙን

FACES
FAMILY AND COMMUNITY ENGAGEMENT SERVICES
4601 W. Bonanza Rd., 2nd Floor
Las Vegas, NV 89107
(702) 799-0303
Fax: (702) 799-0308
Email: faces@interact.ccsd.net
faces.ccsd.net

Like us on Facebook:
www.facebook.com/CCSDFACES

Follow us on Twitter:
@CCSD_FACES

Amharic

## ደረጃ 1

**አዲስ የትምህርት አማማር ከበፊት የትምህርት አማማር እና ልምድ ጋር የተያያዘ ነው።**

### ይህ ምን ማለት ነው?

ይህ ማለት፣ አንድ ተማሪ አዲስ ነገር ከመማሩ በፊት አዲሱን ጽንሰ-ሃሳብ ተማሪው በፊት ከነበረው ልምድ ጋር እንዲያዛምደው ማድረጉ ጉዳዩን በሚገባ እንዲረዳው ያግዘዋል። ይህም አዲሱን የመማማር ሂደት የበለጠ ትርጉም ያለው ያደርገዋል።

### ልጅዎን እንዴት መርዳት ይችላሉ?

ልጅዎ ምን አዲስ ነገር እንደተማረ/ች እና አዲሱ ነገር ለምን እንደሚጠቅም እንዲነግርዎ/እንድትነግርዎ ይጠይቁ።

ለልጅዎ የህይወት ልምድዎን በማጋራት ለየት ያለ የትምህርት አማማር ለትምህርት ቤቱ ያስተላልፉ። ልጅዎን ወደ ሸቀጣ ሸቀጥ መደብር፣ ሙዝየም፣ ፊልም ቤት፣ መናፈሻ ፓርክ፣ የአትክልት ቦታ፣ ወዘተ... ይዘው ይሂዱ።

ወደ ቤተ መፅሐፍት ቤት በመሄድ ልጅዎ የሚፈልጋቸውን መፅሐፍት ይዋሱለት።

ከልጅዎ ጋር በመሆን በቴክኖሎጂ እየታገዛችሁ ስለተያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ምርምሮችን አድርጉ፤ ስለ ርዕሰ ጉዳዩ የተሰሩ ቪዲዮዎች ካሉ ፈልጉ፤ ስለ ርዕሰ ጉዳዩ ያለዎትን እውቀት ለልጅዎ ይንገሩ።

ልጅዎ በተሟላ አስተሳሰብ እንዲናገር ያበረታቱት

ለምሳሌ:

"ዛሬ ____________________ አደረግሁ።"

"አዲስ የተማርኩት ነገር ____________________ነው።"

ልጅዎ ስለ አንድ ርዕሰ ጉዳይ በተመለከተ በተማረው ላይ ያገኛቸውን አዳዲስ መረጃዎች በዝርዝር ማስፈር እንዲጀምር ያድርጉ፤ በየቀኑም ተጨማሪ መረጃዎች ሲገኙ በዝርዝሩ ላይ እንዲካተቱ ይሁኑ።

## ደረጃ 2

**የመማር ተግባሮች ከተለያዩ ተማሪዎች ከፍተኛ የሆነ የአዕምሮ ንቃትን ይፈልጋሉ**

### ይህ ምን ማለት ነው?

ይህ ማለት፣ ተማሪዎች ተገቢ የሆነ የአካደሚክ ሥራዎችን እንዲያገኙ ይደረጋሉ፤ ሆኖም ተማሪዎቹ ምክንያታዊ እንዲሆኑ፣ እንዲያስታውሱ፣ እንዲገነዘቡ፣ እና ችግሮችን እንዲፈቱ ይጠበቃሉ።

### ልጅዎን እንዴት መርዳት ይችላሉ?

ልጅዎ ለአንድ ጥያቄ ከሚሰጠው መልስ ጀርባ ያለውን ምክንያት እንዲያብራራ ወይም መልሱን በተለይ የመረጠበትን ምክንያት እንዲገልጽ ያድርጉ።

ለምሳሌ: "ያንን የሂሳብ ጥያቄ እንዴት ፈታኸው?" "የሳይንስ ፕሮጀክትህን እንዴት እንዳጠናቀቅከው ግለጽልኝ"

ልጅዎ አንድ ጥያቄን ሲፈታ ጥያቄውን ለመመለስ የተከተለውን ሂደት በምስል፣ በቁስአካል በመታገዝ ወይም በስዕላዊ መግለጫ እንዲያብራራ ያድርጉ።

ልጅዎን መልሶቻቸው አዎ ወይም አይደለም ከሚሉ ጥያቄዎች ይልቅ "ማን፣ ምን፣ የት፣ መቼ፣ ለምን እና እንዴት" የሚሉ ጥያቄዎች ይጠይቁ።

ለምሳሌ: "ገጸባህሪው በዚህ መልክ የሚተውነው ለምንድን ነው?" "የዚህኛውን ታሪክ ሌላ ካነበብከው ታሪክ ጋር እያወዳደርክ ማነፃፀር ትችላለህ ወይ?" "ውኃ እንዴት እንደሚተን ግለፅ

ችግሮችን የመፍታት ስትራቴጂዎችን የሚያካትቱ፤ እድሜን የሚመጥኑ ጨዋታዎችን፣ እንቆቅልሾችን እና ፓዝሎች የመገጣጠም ጨዋታዎችን ተጫወቱ።

ለምሳሌ: የቃላት እንቆቅልሾች (ክሮስ ዎርድ)፣ የቃላት ፍለጋዎች፣ ጥያቄና መልስ፣ ዳማ ወይም ቼዝ፣ ሃንግማን፣ ዩኤንኦ(ካርታ መሰል ጨዋታ)፣ የማዛመድ (ተመሳሳዮችን የመፈለግ) ጨዋታዎች፣ ወዘተ...

ልጅዎ እንደቤት ሥራ የተሰጡትን የቃላት ፍች (የቮካብዩለሪ)ጥያቄዎች በመፈተሽ በአፍ መፍቻ ቋንቋችሁ ያሏቸውን ፍችዎች በማስረዳት የቃላቶቹን ትርጉሞች በሚገባ እንዲረዳ ያግዙ።

## ደረጃ 3

**ተማሪዎችን በንግግር እና ሌሎች ስልቶችን በመጠቀም ትርጉም ሰጪ ተግባር ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ**

### ይህ ምን ማለት ነው?

ይህ ማለት፣ ተማሪዎች ወደፊት ስለሚማሩት ነገር፣ አሁን ምን እየተማሩ እንደሆነ እና እስከ አሁን ምን እንደተማሩ  ቆም ብለው መናገር እንዲችሉ ዕድሉን መስጠት ማለት ነው። ይህም ተማሪዎች ስለሚማሩት ነገር ትርጉም በሚገባ እንዲረዱ ያግዛቸዋል።

### ልጅዎን እንዴት መርዳት ይችላሉ?

ከልጅዎ ጋር የሁለት ወገን ውይይት ያድርጉ፤ ውይይቱም ጥያቄ መጠየቅን፣ ዝርዝር ማቅረብን፣ እና ተመሳሳይነት ወይም ልዩነትን መግለጽን ማካተት ይኖርበታል።

ለምሳሌ: በግብይት ወቅት ስለ ዋጋዎቹ፤ ስለ ንጥረ ነገሮቹ ፣ እና በእራት ዝግጅት ሂደት ውስጥ ስለሚካተቱ ቅደም ተከተሎች ተነጋገሩ።

ልጅዎ ከትምህርቱ ያገኘውን ሃሳብ በጽሑፍ መግለጽ እንደ አንድ አማራጭ መንገድ አድርጎ እንዲጠቀም ያበረታቱ።

የቴሌቪዥን ዝግጅት በምትከታተሉበት ወይም መጽሐፍ በምታነቡበት ወቅት ከልጅዎ ጋር ተወያዩ

ለምሳሌ: ልጆችዎ ስለሚወዷቸው ገጸባህሪያት፣ ታሪኩ የት እንደተከናወነ፣ እና በታሪኩ ውስጥ ምን እየተደረገ እንደሆነ ይጠይቋቸው።

ልጅዎን በቤት ውስጥ በሚሰሩ ሥራዎች ላይ ያሳትፉ።

ለምሳሌ: በቤት ውስጥ የሆነ ነገር ሲጠግኑ፣ ምን እያደረጉ እንደሆነ እና ለምን እንደሚያደርጉት ለልጅዎ ይግለጹ። እርስዎ ከመግልጽዎ በፊት፣ ልጅዎ ጥገናው እንዴት ቢከናወን ጥሩ እንደሚሆን ሃሳቦች እንዲስጥ እና እንዴት ጥገናው ሊከናወን እንደሚገባ እንዲገምት ይጠይቁ።

በአንድ ቃል ብቻ ሊመለሱ የሚችሉ ጥያቄዎችን ከመጠየቅ ይቆጠቡ።

ለምሳሌ: "ስለ........ንገረኝ"፣ "ስል ........ምን ታስባለህ"፣ "ይህን ትመርጣለህ ወይስ ........"፣ "........የሆነ ነገር ምንድን ነው"